# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
# የአጠቃላይ ምርጫ እና ኮቪድ ወረርሽኝ ስጋትን አስመልክቶ ለህገመንግስት አጣሪ ኮሚቴ የቀረበ ማብራሪያ

## ስለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፌዴራል እና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻ እና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያከናወን በህገመንግስቱ መሰረት የተቋቋመ ተቋም ነው ። ቦርዱ እንደገና በተቋቋመበት አዋጅ 1133/ 2011 ዓ.ም እና በምርጫ፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች እና ስነምግባር ህግ 1162/2011 ዓ.ም ስር የተሰጡትን ተግባርና ሃላፊነቶች የሚያከናውን ሲሆን እነዚህ ሃላፊነቶች ዋናው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ ማንኛውንም አይነት የምርጫ አይነቶችን እና ህዝበ ውሳኔዎችን ማደራጀት ነው።

ቦርዱ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ አምስት አጠቃላይ ምርጫዎችን፣ አራት የአካባቢ ምርጫዎችን፣ስድስት ህዝበ ውሳኔዎችን እንዲሁም የተለያዩ ማሟያ ምርጫዎችን አከናውኗል። ነሃሴ 23 ቀን 2012 ዓ.ም ሊያከናውነው አቅዶ ለነበረው አገራዊ አጠቃላይ ምርጫ የኦፕሬሽን እቅድ እንዲሁም የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ይፋ አድርጎ እነደነበረ ይታወሳል።

በዚህ እቅድ መሰረት የመራጮች ምዝገባን በ30 ቀናት ውስጥ የእጩዎች ምዝገባን በ14 ቀናት ውስጥ የምረጡኝ ዘመቻን በ90 ቀናት ውስጥ እንዲሁም ለመራጮች የሚሰጥ ትምህርትን ለ 121 ቀናት ያህል ለማከናወን እየተዘጋጀ ነበር። በአንድ ምርጫ ጣቢያ እስከ 1500 እንደሚያስተናግድም ታሳቢ ተደርጓል።

ለአጠቃላይ ምርጫው

- 50 ሚልዮን ያህል መራጮችን ለማሳተፍ
- 50 ሺህ ምርጫ ጣቢያዎችን ለማደራጀት
- 250 ሺህ ምርጫ አስፈጻሚዎችን መልምሎ፣ አሰልጥኖ ለማሰማራት በቦርዱ ዝግጅት እየተደረገ ነበር።

ዝግጅቱ ያተኮረባቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

1. አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ምርጫ ለማከናወን የሚያስፈልገውን በጀት ከመንግስት እና ከአለምአቀፋዊ አጋር ድርጅቶች ማግኘት (securing budget)
2. ለመራጮች ምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ለ50 ሺህ ምርጫ ጣቢያዎች አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች ግዥ መጠናቀቅ ፤
3. በአምስት አገራዊ ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በአፋርኛ እና በሶማሌኛ የተዘጋጁ የመራጮች ምዝገባ ሰነዶች ማሳተም፤

4. የምርጫ ቁሳቁሶቹ እና ሰነዶቹን አስተማማኝ የሆነ ጥበቃ ባለበት መጋዘን ማስቀመጥ፤
5. ለምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ ከተለያዩ ተቋማት የመረጃዎችን ዝርዝር ማሰባሰብ፤
6. የምርጫ ክልሎችን የሚያሳየውን ካርታ በዲጂታል መልክ ማዘጋጀት እና ይፋ ማድረግ፤
7. የምርጫ ጣቢያዎች መረጃ በጂአይኤስ ቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲሰበሰቡ እና ምርጫን ለማከናወን ዝግጁ የሆነ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ/ ማጣራት፤
8. የምርጫ ክልል ቢሮዎች ማደራጀት እና ከክልሎች የሚያስፈልጉ ትብብሮችን ማስተባበር ፤
9. ምርጫ አስፈጻሚዎችን ማሰልጠኛ ስትራቴጂ ማጠናቀቅ፣ የአሰልጣኞች ስልጠና ለማከናወን ዝግጅት መጠናቀቅ፤
10. የምርጫ፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች እና ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011ን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ 28 መመሪያዎችን ማርቀቅ፤
11. በአስራ ሁለት ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ከፓለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪል ማህበራት እና ከሚዲያ ተወካዮች ጋር ውይይቶች ማድረግ፤
12. የመራጮች ትምህርት ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ትምህርቱ በአምስት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በአፋርኛ እና በሶማሌኛ እንዲከናወን ዝግጅት ማድረግ
13. ፖለቲካ ፓርቲዎች በአዲሱ ህግ መሰረት እንዲመዘገቡ ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ዝርዝር ማዘጋጀት እና ለሁሉም ፓርቲዎች ማሳወቅ እና ያስገቧቸውን ሰነዶች መገምገም
14. ከሲቪል ማህበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ውይይቶችን ማድረግ፤

ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት እየተከናወኑ ባሉበት ወቅት መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም የኮቪድ 19 የመጀመሪያው ኬዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በመገኘቱ መንግስት መጋቢት 07 ቀን 2012 ዓ.ም ላይ የመጀመሪያውን የ14 ቀን ክልከላ ይፋ አደረገ፣ ቦርዱም ይህንኑ የሁለት ሳምንት ክልከላ ተከትሎ የኮቪድ19 ወረርሽኝ ስጋት እና ክልከላዎቹ በምርጫ ኦፕሬሽን ላይ ሊኖራቸው ስለሚችለው ተጽእኖ ዳሰሳ ጥናት መስራት ጀመረ። በጥናቱ የመጀመሪያ ግኝቶች ላይ መሰረት አድርጎም መጋቢት 11 ቀን 2012 ዓ.ም ከፓለቲካ ፓርቲዎች ጋር ውይይት አድርጓል።

ቦርዱ በመጋቢት ወር የኮቪድ ወረርሽኝ ስጋትን ተከትሎ ያስጠናው ጥናት አለም አቀፍ የወረርሽኙን አዝማሚያ (Trend)፣ አገራዊ ነባራዊ ሁኔታን፣ የማህበረሰብ ጤና ባለሞያዎች ግብአትን እና የክልከላዎቹ አይነቶች ምርጫ ላይ የሚያድርሱትን ተጽእኖ ባካተተ መልኩ የተደረገ ነው።

በዚህም መሰረት በክልከላው ለሁለት ሳምንት ብቻ ቢቆይ ወደተቋረጡ ስራዎች ተመልሶ ምርጫን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ማከናወን የሚቻል መሆኑን የመጀመሪያው ሴናሪዮ ያሳየ ሲሆን ሁለተኛው ሴናሪዮ ደግሞ ክልከላዎቹ በወቅቱ ከነበረው የሁለት ሳምንት ክልከላ በተጨማሪ ቀናት ከቀጠሉ ግን ምርጫውን ለማካሄድ እንደማይቻል አሳይቷል። በወቅቱ በክልሎች ከተጣለው ተጨማሪ ክልከላ፣ ከጤና ባለሞያዎች በተሰጠው ሞያዊ አስተያየት በመነሳት ምርጫውን በወቅቱ ለማካሄድ እንደማይችል ወስኗል። በውሳኔውም ቦርዱ የወረርሽኙ ሥጋት ተወግዶ ሁኔታዎች ሲመቻቹ እንደገና ግምገማ በማድረግ አዲስ የምርጫ ኦፕሬሽን እቅድና ሰሌዳ በማውጣት

እንቅስቀሴውን እንደሚያስጀመር ለተወካዮች ምክር ቤት ያሳወቀ ሲሆን በወረርሽኙ ስጋት የማይስተጓጎሉ ስራዎችን እንደሚሰራም ገልጾ ነበር ።

## ቦርዱ አሁን እየሰራቸው ያሉ ተግባራት

መጋቢት 22 ቀን 2012 ዓ.ም. የምርጫ ስራው መታገዱ ይፋ ከተደረገ በኋላ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ቀጣይነት ያላቸው የአሰራር ሂደት እቅዶችን፣ የግንኙነት ፕሮቶኮሎችን እንዲሁም ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የስራ ቅደም ተከተሎችን በድጋሚ ነድፏል። ቦርዱ በዋናነት ከምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ ግንኙነቶችን በቀጣይነት በማድረግ ምርጫውን በተመለከተ ቀጣይ ስራዎች ላይ እያተኮረ ይገኛል።

ከምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረዝ በኋላ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት

1. የመራጮች ምዝገባን ወደ ዲጂታል መረጃ በመቀየር የሚያስችል ለድምጽ መስጫ ቀን ዝግጅት የሚረዳ ዳታቤዝ ግንባታ
2. የእጩዎች ምዝገባን ወደ ዲጂታል መረጃ ለመቀየር የሚያስችል ዳታቤዝ ግንባታ
3. የእጩ ወኪሎች ሲቪል ማህበራት ታዛቢዎችን እና እውቅና የተሰጣቸው ጋዜጠኞችን መረጃዎች ወደዲጂታል ለመቀየር የሚያስችል ዳታቤዝ ግንባታ
4. ምዝገባቸውን ለማጠናቀቅ ሰነዶችን ያስገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰነዶች ማጣራት እና ውሳኔዎችን ማሳለፍ
5. ለድምጽ መስጫ ቀን አገልግሎት ላይ የሚውሉ ግዥዎች ማከናወን፣ በዚህም መሰረት የሚስጥር ድምጽ መስጫ ሳጥን፣ ለድምጽ መስጫ ቀን የሚያገለግሉ የምልክት ቀለሞች፣ የጽህፈት መሳሪያዎች ግዥ ተጠናቆ ወደአገር በመግባት ላይ ይገኛል።
6. ለድምጽ መስጫ ቀን የሚውሉ ቁሳቁሶች ተጨማሪ መጋዘን በማስፈለጉ፣ ይንው የተጨማሪ መጋዘን ዝግጅት ተጠናቋል።
7. የመራጮች ትምህርት ለሚሰጡ የሲቪል ማህበራት እውቅና ለመስጠት ሰነዶች ግምገማ እየተካሄደ ነው
8. በአምስት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮሚኛ ፣ በትግርኛ፣ በሶማሊኛ እና በአፋርኛ የሚዲያ ክትትል ለማከናወን የሚዲያ ክትትል እቃዎች ግዥ እየተከናወነ ነው ።
9. የሚዲያ ክትትል የሚያደርጉ ሰራተኞች ቅጥር እየተከናወነ ነው።።
10. የሚዲያ ሴንተር ለማቋቋም ጥናት ተከናውኖ ተጠናቋል።

## የወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ቦርዱ ለወደፊት ሊከተላቸው የሚችላቸው የምርጫ አፈጻጸም አቅጣጫዎች

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ አንፃር ቀጣይ በቀጥታ በምርጫ ጋር የተገናኙ የአሰራር እቅድ ሲናሪዎችን በተከታታይ እየገመገመ ይገኛል። ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምላሽ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች ለምርጫ አፈጻጸም ሂደት ተግዳሮት እንደፈጠሩ ይታወቃል። በተለይ ደግሞ በአገራችን ተግዳሮቶቹ

ከፍተኛ የሆኑበት ምክንያት የምርጫ ሂደቱ ዋና ዋና ስራዎች በተለይም የመራጮች ምዝገባ፣ የእጩ ምዝገባ እንዲሁም ድምፅ አሰጣጥ በአነስተኛ የቴክኖሎጂ እገዛ የሚከናወኑ በመሆናቸው ነው። የምርጫ ስራው ስፋት፣ ካሉት የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች እንዲሁም የደህንነት እና የልማት ሁኔታ አንጻር ሲታይ በሌሎች አገሮች እየተተገበሩ ያሉ በኦንላይን መራጮችን መመዝገብ፣በፖስታ ድምፅ የመስጠት እና የኤሌክትሮኒክ ድምጽ አሰጣጥ የመሳሰሉትን ለመተግበር ፍጹም አመቺ አይደለም።

## የቦርዱ የግምገማ ሂደት

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የወደፊቱን አቅጣጫ ለማስቀመጥ በሶስት ክፍሎች ግምገማውን እያከናወነ ይገኛል። በመጀመሪያው ክፍል ስጋቶችን እና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎችን ያየ ሲሆን በሁለተኛ ክፍል እነዚህ ስጋቶች በኦፕሬሽን እና በበጀት ላይ ያላቸውን እንድምታ ለማወቅና በዚህ ሪፓርትም ለማሳየት ተሞክሯል። በሶስተኛ ክፍል እነዚህን እንድምታዎች ከአገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር የሚያደርግባቸው ይሆናል።

## ሂደቱን በመገምገም ወቅት የተወሰዱ ግምቶች

ቦርዱ የወደፊቱ የምርጫ ሁኔታ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን በሚያይበት ወቅት ከኮቪድ 19 እና ከምርጫ ስራዎች ጋር የተያያዙ አደጋዎች ፣ተፅእኖዎች እና ምላሾችን መለየት ላይ የሚያተኩሩ ግምቶችን ወስዷል። ግምቶቹን መነሻ አድርጎም ተግዳሮቶቹ በምርጫ አፈጻጸም ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ በሁለት ሲናሪዎች ለይቶ አስቀምጧል። እነዚህ ከስር የሚታዮ ግምቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍል የተከፈሉ ናቸው። በመጀመሪያው ክፍል የሚታዩት አጠቃላይ ግምቶች ሲሆኑ ሁለተኛው ክፍል የሚታዩት ደግሞ ቀጣይነት ያለው የኮቪድ19 ከፍተኛ ወረርሽኝ ስርጭት ቢኖር በሚል የተወሰዱ ናቸው።

### <u>አጠቃላይ ግምቶች</u>

1. በተለምዶ በምርጫ አሰራር እቅድ ውስጥ በዋናነት የማይሳተፉ ባለድርሻ አካላት ቁልፍ ባለድርሻዎች ይሆናሉ።እነዚህም የጤና ሚኒስትር እና ጤና ቢሮዎች፣ የጤና ባለሙያዎች (ኢፒዲሞሎጂስት እና የመሳሰሉት) እንዲሁም እንደ የአለም ጤና ድርጅት የመሳሰሉት አለም አቀፍ ድርጅቶች ናቸው።
2. በጊዜ ሰሌዳው ላይ የሚታዩ የተለያዩ የምርጫ ሂደቶች የሚወስዱት ጊዜ ሊጨምር ይችላል
3. መደበኛው የአቅርቦት ሰንሰለት በመዛባቱ ምክንያት የተፈላጊ የምርጫ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች ዋጋ ሊጨምር ይችላል።
4. ከመንግስት በጀት የሚገኘው ገንዘብ አነስተኛ ሊሆን እና ከአለምአቀፍ አጋሮች ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘትም እንቅፋት ሊያጋጥም ይችላል
5. ኮቪድ 19 ሊኖረው የሚችለው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ማህበራዊ ውጥረቶችን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ሊጨምር እና በዚህም የተነሳ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ያለመረጋጋት ስጋቶችን ሊከሰቱ ይችላሉ።

**ቀጣይነት ካለው ኮቪድ 19 ከፍተኛ ስርጭት ጋር የተያያዙ ግምቶች**

6. የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ እና በአንድ አካባቢ የሚሰበሰቡ ሰዎች ቁጥር ላይ ገደብ ማድረግ የምርጫ ስራዎች በሚከናወኑት ጊዜ ላይም በተወሰነ መልኩ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ
7. ከኮቪድ 19 በኋላ ያሉ ሁኔታዎች በምርጫ ስራዎች ላይ አዳዲስ እርምጃዎችን እና መመዘኛዎችን ማስተዋወቅን ሊያስገድዱ ይችላሉ። (ለምሳሌ የአካል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ ከአልኮል የተሰሩ የእጅ ማጽጃዎች፣ የፀረ-ተህዋሲ ርጭት ማድረግ የመሳሰሉት ይገኙበታል።)
8. የልዩ ልዩ እርምጃዎች አፈፃፀምን አስመልክቶ የምርጫ ህግ ማእቀፎች ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ።
9. የኮቪድ 19 ፍራቻ በዜጎች ምርጫ ተሳትፎ ላይ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል።
10. የተወሰኑ ህብረተሰብ ክፍሎች በቫይረሱ እና በተዛማጅ የማህበረሰብ ጤና እርምጃዎች የተነሳ ከሌላው ህብረተሰብ በተለየ ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችል ሲሆን ይህም አካታችነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

## ሁለቱ ሲናሪዎች

ከላይ የተዘረዘሩትን ግምቶች መሰረት በማድረግ ቦርዱ ሁለት የጊዜ ሰሌዳን የሚያሳዩ ሁኔታዎችን ቦርዱ አዘጋጅቷል።

**የመጀመሪያው ሲናሪዎ**

በዚህ ሲናሪዎ መሰረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተጨማሪ ልዩ እርምጃዎችን ሳይወስድ ምርጫውን የሚያካሄድ ሲሆን በክፍል ሁለት የተዘረዘሩት ግምቶችም አይተገበሩም። ሆኖም ግን የምርጫው የጊዜ ሰሌዳ መሰረዙ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ በምርጫ ቦርዱ አቅም ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል። በተጨማሪም ሌሎች ለምርጫ ስራ ትብብር ማድረግ የሚጠበቅባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች (national authorities) በመላው ሀገሪቱ ወረርሽኙን አስመልክቶ የመስክ ስራዎችን የሚያከናውኑ በመሆኑ ይህ በተወሰነ መልኩ አቅማቸውን የሚገድብ እና ትኩረታቸውንም ከምርጫ ስራ ውጪ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። በዚህም የተነሳ ቦርዱ ከሌሎች ተቋማት የሚያገኘው ድጋፍ ይቀንሳል።

ከዚህ በላይ በተገለጸው ምክንያት ለምርጫ ስራ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ መስሪያ ቤቶች ይህንን ድጋፋቸውን መልሰው ለመቀጠል የሁለት ወራት ጊዜ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ገምቷል። በተጨማሪም አጠቃላይ የጊዜ ሰሌዳው በመራዘሙ ምክንያት ቦርዱ ለተጨማሪ ወጪዎች ይዳረጋል። ተጨማሪ ወጪዎቹ በአብዛኛው የሚያያዙት ከተሻሻለ የመራጮች ትምህርት እና ሎጅስቲክስ ስራዎች ጋር ነው።

በዚህም መሰረት ዋና ዋና የምርጫ ተግባራት በሚከተለው ሁኔታ ሊቀየሩ ይችላሉ።

**ተቋማዊ ሁኔታ-** ተቋማዊ ስራን በተሟላ ሁኔታ ለመጀመር ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልጋል። ምርጫውን ለመደገፍ የሚሳተፉ አካላትን ሙሉ ተሳትፎ እና ትኩረት ለማግኘት እንዲሁም የምርጫ ስራን ዋናና ቀዳሚ አጀንዳ ለማድረግ **60 ቀናት** ይወስዳል።

**የመራጮች ምዝገባ እና የእጪዎች ምዝገባ** -በዚህ ሲናሪዮ መሰረት በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተሻሻለ የመራጮች ትምህርት ዘመቻ አስፈላጊ ይሆናል። ይህም የሚሆነው ምንም እንኳን የወረርሽኙ ስጋት ባይኖርም የመራጮች ተሳትፎ በስጋት እንዳይገታ ተጨማሪ የመራጮችን ስጋት የሚቀንስ የመራጮች ትምህርት ስለሚያስፈልግ ነው።

የምርጫው የጊዜ ሰሌዳ በመሰረዙ የማከማቻ መጋዘን ወጪ፣ እንዲሁም ደሞ የመራጮች ትምህርት ተጨማሪ ይዘቶች ስለሚኖሩት ተጨማሪ የማስፈጸሚያ ወጪ ይኖረዋል። በሌላ በኩል የእጩዎች ምዝገባ ተለይቶ የሚከናወን ይሆናል ማለት ነው። በአጠቃላይ ይህ ተግባር **76 ቀናት** የሚፈጅ ይሆናል።

**የምረጡኝ ዘመቻ** - በኮቪድ 19 እገዳዎች የተነሳ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊዎቻቸውን ለማግኘት እና ለማደራጀት አልቻሉም። ስለሆነም በምርጫ ወቅት ፓርቲዎቹ ረዘም ያለ የቅስቀሳ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በዚህም ምክንያት የምረጡኝ ዘመቻ በአጠቃላይ **102 ቀናት** ይፈጃል።

**ድምጽ መስጠትና ቆጠራ -** በድምጽ መስጫ እለት ድምጽ የሚሰጡ ዜጎች ቁጥራቸው እነዳይቀንስ እና የመራጮች ተሳትፎ እንዳይገደብ ተጨማሪ ከኮቪድ ጋራ የተያያዘ ይዘት ያለው የመራጮች ትምህርት ያስፈልጋል።። ለዚህ ተጨማሪ ሁኔታ ተጨማሪ በጀት ያስፈልጋል።

በዚህ የመጀመሪያ ሲናሪዎ አጠቃላይ ምርጫው ለማስፈጸም የሚያስፈልገው **ተጨማሪ በጀት** መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ብር (139,349,918) ይሆናል። ይህም በዶላር ሲሰላ አራት ሚልዮን ዘጠና ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃያሰባት ሺህ (4, 098,527) ዶላር ይሆናል። ለዝግጅት የሚያስፈልገው ጊዜ አስር ወር ይሆናል።

**ሁለተኛው ሲናሪዎ**

በሁለተኛው ሲናሪዎ የታየው ኮቪድ 19 በኢትዮጵያ የሚቀጥል ሆኖ ምርጫ ቦርድም በተወሰኑ ገደቦች ስር ምርጫውን የሚያከናውንበት ሁኔታ ይኖራል በሚል ነው። የምርጫው መታገድ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ ቦርዱ እና ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በሙሉ አቅም ስራቸውን የመስራት ሁኔታ ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል። በተጨማሪም ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች ኮቪድ 19'ን ለመግታት በሚደረገው እንቅስቃሴ ስለሚዋጡ ለምርጫ ዝግጅቶች የሚውለው ሀብት እና አቅም ይቀንሳል።

የልዩ እርምጃዎች አፈጻጸሙ በምርጫ ጊዜ ሰሌዳው (የመራጮች ምዝገባ፣ የእጩ ምዝገባ፣ ምረጡኝ ቅስቀሳ እና የድምፅ መስጫ ወረቀቶች የማተም ዝግጅት) ላይ የመራዘም ተፅእኖ ይፈጥራል። በተጨማሪም በምርጫ በጀቱ ላይ ጉልህ ተጽእኖ ይኖረዋል።

በዚህም መሰረት ዋና ዋና የምርጫ ተግባራት በሚከተለው ሁኔታ ሊቀየሩ ይችላሉ።

**ተቋማዊ ሁኔታ** - ምርጫውን ለመደገፍ እና ለማስተባበር ፣ ሊሳተፉ የሚችሉ ተቋማትን ተሳትፎ ለማስቀጠል እና የትብብር አሰራሩን ለመዘርጋት እንዲሁም በተጨማሪ አዲስ መሳተፍ ያለባቸው ከጤና ጋር የተገናኙ የመንግስት ተቋማት እና ባለሞያዎቻቸውን ድጋፍ ለማግኘት የሚስችል አሰራር ስርአት ለመዘርጋት ተጨማሪ ጊዜ ይፈልጋል። ከዚህ አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስራዎችን ለመለየት እንዲሁም ጤናን መሰረት ያደረጉ ህጎች እና መመሪያዎችን ለማዘጋጀት እና ለማጽደቅ ተጨማሪ **90 ቀናት** የዝግጅት ጊዜ ይወስዳል።

**የመራጮች ምዝገባ-** ለመራጮች ምዝገባ የሚደረጉ ዝግጅቶች በጤና ፕሮቶኮሎች ምክንያት በአነስተኛ መጠን ብቻ የሚደረጉ ሲሆን ይህም የአሰልጣኞች ስልጠናን እና የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠናን በተገደበ ቁጥር ነገር ግን በተራዘመ ጊዜ እንዲደረግ ሁኔታው ያስገድዳል።

በአንድ ምርጫ ጣቢያ የሚመዘገቡ መራጮች ቁጥር በ1000 ሰዎች የሚገደብ ይሆናል ፤ በዚህም ምክንያት የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር በ10 ሺህ ይጨምራል፣ ተጨማሪ የሥልጠና ጊዜ እና ወጪ እነዲሁም የምርጫ ማስፈፀሚያ ቁሳቁሶች ግዥ አስፈላጊ ይሆናል። ለነዚሁ10 ሺህ ምርጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈጻሚዎችን መመልመል እና ማሰልጠንም ያስፈልጋል። ይህም ማለት ቀድሞ ከታቀደውን የአስፈጻሚዎች ቁጥር በ30 ሺህ እነዲጨምር ያደርገዋል።

በመራጮች ምዝገባ ወቅት ለምርጫ አስፈፃሚዎች የግል ደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎች እና ለመራጮች የንፅህና መጠበቂያ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል። የመራጮች ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅትም ከምርጫ አስፈጻሚዎች በተጨማሪ ለእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የጤና ጥንቃቄዎችን የሚያስፈጽም አንድ ተጨማሪ ሰው የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም በአንድ ምርጫ ጣቢያ የአስፈጻሚዎችን ቁጥርን ወደ አራት ከፍ ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የሚፈለገው የሰው ሃይል ቁጥሩ ከ180 ሺህ ወደ 240 ሺህ ሰው ከፍ ይላል።

የማህበራዊ ርቀትን ለመጠበቅ ሲባል የመራጮች ምዝገባ ቀን ከ30 ቀናት ወደ 45 ቀናት የሚጨምር ይሆናል። የእቃዎች እሽጋ ስራም ማህበራዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ ስለሚከናወን ተጨማሪ ጊዜ ይወስዳል። እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ተካተው የመራጮች ምዝገባ ሂደት **55 ቀናት** የሚፈጅ ይሆናል።

**የእጩዎች ምዝገባ** - ለቦርዱ ሰራተኞች እና ለእጩ ተወዳዳሪዎች በእጩዎች ምዝገባ ወቅት የአካል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች ያስፈልጋቸዋል። ሊፈጠር የሚችለውን መጨናነቅ ለመቀነስ ሲባል የእጩዎች ምዝገባ ከመራጮች ምዝገባ በኋላ የሚካሄድ ይሆናል፣ በአጠቃላይም **21 ቀናት** ይፈጃል።

**የምረጡኝ ዘመቻ -** በኮቪድ 19 ገደቦች ምክንያት የፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊዎቻቸውን ለማደራጀትም ሆነ ለማግኘት ባለመቻላቸው ለምረጡኝ ዘመቻ ረዘም ያለ ጊዜ ያስፈልጋል፣ በመሆኑም የምረጡኝ ዘመቻ በአጠቃላይ **128 ቀናት** የሚፈጅ ይሆናል።

**ድምጽ መስጠትና ቆጠራ** - በድምጽ መስጫ ቀን ከአምስት የምርጫ አስፈጻሚዎች በተጨማሪ ሁለት የጤና ጥንቃቄ አስፈጻሚ እና ሰልፍ ተቆጣጣሪ ሰራተኞች በአጠቃላይ ሰባት አስፈጻሚዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን በተጨማሪነት ከሚከፈቱት 10 ሺህ ምርጫ ጣቢያዎች ጋር በአጠቃላይ 420 ሺህ አስፈጻሚዎች ያስፈልጋሉ።

ከዚህም በተጨማሪ በድምጽ መስጫው ቀን ለነዚሁ አስፈጻሚዎች የአካል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች የሚያስፈልጉ ሲሆን ለድምጽ ሰጪዎች ደግሞ የንጽህና መጠበቂያ አልኮል/ሳኒታይዘር በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች መዘጋጀት ይኖርበታል።

ለተጨማሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች ግዥ እንዲሁም መራጮች ለኮቪድ ወረርሺኝ ሳይጋለጡ ድምጻቸውን የሚሰጡበት በጣም ሰፊ የጤና ይዘትን ያካተተ የመራጮች ትምህርት አስፈላጊ ይሆናል። ለምርጫው ደህንነት ሲባል የድምጽ አሰጣጥ በከፍተኛ ጥንቃቄ በአንድ ቀን ውስጥ የሚከናወን ይሆናል።

ይሄ ሁለተኛው የኮቪድ የጤና ጥንቃቄን አካቶ የሚደረገው የምርጫ ሂደት ከላይ ለተጠቀሱት ስራዎች ብቻ ሁለት ቢልዮን አምስት መቶ አስራሁለት ሚልዮን ዘጠኝ መቶ ሃያስድስት ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት / 2,512,926,536 / ብር ወይም ሰባ ሶስት ሚልዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አራት ዶላር /73, 909,604/ ተጨማሪ በጀት የሚያስፈልገው ሲሆን በአጠቃላይ አስራ ሶስት ወራትን የሚፈጅ ሂደት ይሆናል።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከላይ የቀረቡትን ሲናሪዎዎች ሲሰራ ከግምት ያስገባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ቢኖሩም በተጨማሪ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ዘንድ ማለትም ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እንዲሁም ከሲቪል ማህበራት ጋር ምክክር በማድረግ ግብአት እና አስተያየቶችን የሚወስድ ይሆናል። ግብአቶቹም ከላይ የቀረቡት ሲናሪዎዎች አፈጻጸም እና ተግባራዊነት ላይ ተጽእኖ ሊኖራቸው ይችላል፣ ከዚህም ባለፈ በሂደት የሚመጡ እዚህ ውስጥ ያልተካተቱ የተለያዩ ነገሮች ቢከሰቱ የምርጫ ኦፐሬሽን ስራው ያንንም ያካተተ መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም የተከበረው የህገመንግሰት አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን ገለጻ ከግምት ውስጥ ሲያስገባ ተግባራዊ አሰራሩ የሌሎች አካላትን አስተያየት ተመርኩዞ ሊቀየር የሚችል መሆኑን እንዲረዳልን  በአክብሮት እንጠይቃለን።

# የቢሆን ሁኔታን የሚያሳዩ አባሪ ሰንጠረዦች

| የቢሆን ሁኔታ ግምት 1፡ ከኮቪድ 19 ጋር የተያያዙ ገደቦች ይኖራሉ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ የምርጫ ሂደቶች** | **በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚኖረው ተፅእኖ** | **ትኩረት የሚፈልጉ የህግ ጉዳዮች** | **የበጀት እንድምታ** | **የጊዜ እንድምታ** | |
| **ተቋማዊ** | ተጨማሪ ጊዜ ይፈልጋል፡- ምርጫውን ለመደገፍ የተሰተፉትን አካላት በድጋሚ ማሰተፍ እንዲሁም የትብብር አሰራሩን እንደገና ማቋቋም - በባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት እና ቅድሚያ መስጠት | የለም | $50,000 | እንደገና ለመጀመር የ2 ወር ጊዜ | |
| **የመራጮች ምዝገባ** | በተራዘመ የጊዜ ሰሌዳ ምክንያት ለተራዘመ ጊዜ የማከማቻ ቦታ እና ለተጨማሪ የመጋዘን ማከማቻ ወጪ መዳረግ | የለም | $2,000,000 | ማህበራዊ ርቀትን ለመጠበቅ እና ሌሎች ገዳቢ እርምጃዎችን መሰረት በማድረግ ለእሽጋ የተወሰኑ ተጨማሪ ቀናት | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተሻሻለ የመራጮች ትምህርት ዘመቻ ፡<br>ሰፊ ሽፋን እና ጥልቀት ያለው መልእክት እንዲሁም ኮቪድ 19’ን የተመለከቱ ይዘቶችን ያካተቱ መልእክቶች | የስልጠና ማኑዋሎችን እና ቁሳቁሶችን ማዳበር | $1,000,000 | የቅስቀሳ ዘመቻ ጊዜ እንደተጠበቀ ይሆናል | |
| **የእጩዎች ምዝገባ** | | የለም | | | |
| **የምረጡኝ ዘመቻ** | በኮቪድ 19 እገዳዎች የተነሳ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድምፅ ሰጪዎችን ለማንቀሳቀስ/ ለማደራጀት አልቻሉም። ስለሆነም ረዘም ያለ ተጨማሪ የቅስቀሳ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። | የመንግስት የጤና ደህንነት ፕሮቶኮሎች የተወሰኑ ልዩ መስፈርቶች ካላቸው እነሱን ለማካተት በመመሪያዎች ላይ ለውጦች ሊኖሩ ይችላሉ። | 0 | አካታችነትን ለመጨመር የጤና ፕሮቶኮሎችን የተከተለ ረዘም ያለ የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ ጊዜ | |
| **ምርጫ እና ቆጠራ** | የተሻሻለ የመራጮች ትምህርት ዘመቻ ፡-<br>ይህም ሰፊ ሽፋን እና ጥልቀት ያለው መልእክት እንዲሁም ኮቪድ 19’ን የተመለከቱ ይዘቶችን ያካተቱ | ተጨማሪ የማስታወቂያ እና | $1,000,000 | የለም | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መልእክቶችን ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግን ይጨምራል | የአየር ሰአት ያስፈልጋል | | | |

| የቢሆን ሁኔታ ግምት 2፡ የኮቪድ 19 ስርጭትን መቆጣጠር ፡ የልዩ ልዩ እርምጃዎች አፈፃጸም | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቁልፍ የምርጫ ሂደቶች** | **በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ** | **ትኩረት የሚፈልጉ የህግ ጉዳዮች** | **የበጀት እንድምታ** | **የጊዜ አንድምታዎች** | |
| **ተቋማዊ** | ተጨማሪ ጊዜ ይፈልጋል፡- ምርጫውን ለመደገፍ እና ለማስተባበር የተሳተፉትን አካላት በድጋሚ ማሳተፍ እንዲሁም የትብብር አሰራሩን እንደገና ማቋቋም -<br><br>በባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መለየት እና ቅድሚያ መስጠት እንዲሁም ቅድሚያ በመስጠት ማስተዳደር | የለም | $100,000 | 3 ወር | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከኮቪድ 19 ጋር በተያያዘ የሚመለከታቸው አካላትን ( እንደ ኢፒዲሞሎጂስት እና የጤና ባለሙያዎችን ያሉትን) የእቅዱ ሂደት ዝርዝር ውይይት ውስጥ በማሳተፍ ማወያየት | የለም | $20,000 | | |
| **የመራጮች ምዝገባ** | በአነስተኛ ስብሰባዎች መጠን ምክንያት የአሰልጣኞች እና የስልጠና ቀኖች ቁጥር መጨመር | የለም | $5,700,000 | 30 የስልጠና ቀኖች | |
| | በአንድ ምርጫ ጣቢያ የሚስተናገዱ የመራጮችን ቁጥርን በ 1000 መገደብ፤ በዚህም ምክንያት የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር መጨመር (10,000 ተጨማሪ ጣቢያዎች) ተጨማሪ የሥልጠና እና የምርጫ ማስፈፀሚያ ቁሳቁሶች ግዥ | የመመሪያ ለውጥ እንደሁኔታው ሊያስፈልግ ይችላል | $1,670,000 | የ 2 ወር ጊዜ ለቁሳቁስ ግዥ እና ማስረከቢያ (መልሶ የማስጀመሪያ ጊዜ አካል) | |
| | ለምርጫ አስፈፃሚዎች የግል ደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎች እና ለመራጮች የንፅህና መጠበቂያ እርምጃዎች | በመመሪያዎች ውስጥ የመከላከያ | $11,300,000 | የ 2 ወር ጊዜ ለቁሳቁስ ግዥ እና ማስረከቢያ (መልሶ የማስጀመሪያ ጊዜ አካል) | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | እርምጃዎችን ማካተት | | | |
| | መጨናነቅን ለመገደብ: የመራጮችን ምዝገባን ለ15 ቀናት ማራዘም ፤ረዘም ያሉ የስራ ውሎች፤ ተጨማሪ ሰራተኞች ማዘጋጀት (ሰልፍን ለማስተዳደር እንዲሁም አዲስ ለተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች ) | የመመሪያ ለውጥ እንደሁኔታው ሊያስፈልግ ይችላል | $40,000,000 | 15 ቀን ጭማሪ: 45 ቀን የመራጮች ምዝገባ እና 10 ቀን በይፋ ወጥቶ ለህዝብ በግልፅ እንዲያየው ለማድረግ | |
| | የምርጫው መታገድ የረጅም ጊዜ የማከማቻ ቦታ ፤ ተጨማሪ ቦታ እና ለመጋዘን አያያዝ አገልግሎቶች የደህንነት ፕሮቶኮሎችን የማቋቋም ፍላጎት አስከትሏል | የለም | $2,100,000 | ማህበራዊ ርቀትን ለመጠበቅ እና ሌሎች ገዳቢ እርምጃዎችን መሰረት በማድረግ የምርጫ ቁሳቁሶችን ለማሸግ የተወሰኑ ተጨማሪ ቀናት | |
| | የተሻሻለ የመራጮች ትምህርት ዘመቻ ፡<br>ሰፊ ሽፋን እና ጥልቀት ያለው (ዘልቆ መግባት የሚችል) መልእክት እንዲሁም ኮቪድ 19’ን የተመለከቱ ይዘቶችን ያካተቱ መልእክቶች | መመሪያዎችን የማሻሻል አስፈላጊነት ለመገምገም ከጤና ባለሙያዎች ጋር መነጋገር | $1,500,000 | ለመራጮች ትምህርት ዘመቻ ረዘም ያለ ጊዜ መስጠት፣ ቢያንስ ከመራጮች ምዝገባ 30 ቀን ቀድሞ ተጀምሮ እስከ የመራጮች ምዝገባ 45ተኛ ቀን እና ይፋ የማድረጊያ ጊዜ 10ኛ ቀን ድረስ እንዲቆይ ማድረግ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የዕጩዎች ምዝገባ** | ለቦርዱ ሰራተኞች እና ለእጩ ተወዳዳሪዎች በእጩ ምዝገባ ወቅት የአካል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች | የመንግስት የጤና ተቋማት ፕሮቶኮሎች ልዩ መስፈርቶች ካሏቸው የመመሪያ ለውጥ ሊያስፈልግ ይችላል | $48,527 | መጨናነቅን ለማስቀረት የዕጩዎች ምዝገባ የመራጮች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ይጀምራል | |
| **የምረጡኝ ዘመቻ** | በኮቪድ 19 ገደቦች ምክንያት የፖለቲካ ፓርቲዎች ድምጽ ሰጪዎችን ለማንቀሳቀስ ባለመቻላቸው ለምረጡኝ ዘመቻ ረዘም ያለ ጊዜ ማስፈለግ | የመንግስት የጤና ተቋማት ፕሮቶኮሎች ልዩ መስፈርቶች ካሏቸው የመመሪያ ለውጥ ሊያስፈልግ ይችላል | 0 | አካታችነትን ለመጨመር የጤና ፕሮቶኮሎችን የተከተለ ረዘም ያለ የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ ጊዜ | |
| **ምርጫ እና ድምጽ ቆጠራ** | ተጨማሪ 10,000 የምርጫ ጣቢያዎች ፡ ተጨማሪ ሠራተኞች (2 ሰልፍ ተቆጣጣሪዎችን ጨምሮ) | የመንግስት የጤና ተቋማት ፕሮቶኮሎች ልዩ | $6,400,000 | የለም | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | መስፈርቶች ካሏቸው የመመሪያ ለውጥ ሊያስፈልግ ይችላል ለምሳሌ ስለ ቀለም አቀባብ | | | |
| | ለምርጫ አስፈጻሚዎች የአካል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሁም ለመራጮች የንፅህና መጠበቂያ እርምጃዎች | መመሪያዎች ውስጥ የጤና ድንጋጌዎችን ማካተት | $2,097,600 | የለም | |
| | ተጨማሪ 10,000 የምርጫ ጣቢያዎች ፤ ተጨማሪ የምርጫ ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ | የለም | $1,474,477 | የለም | |
| | የተሻሻለ የመራጮች ትምህርት ዘመቻ:-<br><br>ሰፋ ያለ ሽፋን እና ጥልቀት ያለው/ዘልቆ መግባት የሚችል/ እና ለአጠቃላይ ህዝቡ እና ለአደጋው ተጋላጭ የሆኑ ወገኖችን ተደራሽ የሚያደርግ ስለ ኮቪድ 19 ተጨማሪ መልክት የያዘ | ተጨማሪ ማስታወቂያዎች እና የአየር ሰአት ያስፈልጋል | $1,500,000 | የለም | |